# ርዕስ፦ „ወቅታዊዉ የሕዝብ ትግል ሲመረመር“

(ወቅታዊዉን የሕዝብ ትግል በብዥታ ዉስጥ ያቆዩት ፖለቲካዊ የስበት ሀይሎች)

## ክፍል-1

(ለኢትዮጵያዉያን ዉይይት እንዲረዳ ታስቦ በግል የተዘጋጀ)

(ይህ ጽሁፍ በሚቀርቡ አስተያየቶች መሰረት ሊሻሻል የሚችል ነዉ።)

ዮሓና-ከፍራንክፈርት

ነሐሴ / ፳፻፱ ዓ/ም፣ (August-2017 - አዉሮፓ)

**መግቢያ፣- ሥራዉን ከመጀመርህ በፊት አብረዉህ ካሉት ጋር በመወያየት መግባባት መፍጠርህን አረጋግጥ!**

## ለግንዛቤ ቁ.1 ፣- ይህን መጣጥፍ ለማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

የተከበሩ አንባቢ ሆይ!፣- በተለያዩ ጊዜያት የአገርዎን አንገብጋቢ ጉዳዮች በማንሳት ከቅርብ ወገኖችዎና ጓደኞችዎ ጋር ዉይይቶችን አድርገዉ ያዉቃሉ? እናም በነዚህ ጊዜያት ያጋጠሙዎት አስገራሚና አንዳንዴም አስደንጋጭ መልሶችና አመለካከቶች በህሊናዎ ጥያቄን ፈጥሮና እረፍትም ነስቶዎት ይሆን? በዚህም ምክንያት ይህ አጣብቂኝ ዉስጥ የገባዉ የዛሬዉ ትዉልድ በተምታታ የሕይወት ጉዞ ላይ እንደሆነ ሲመለከቱስ የተረበሸ ስሜት አልፈጠረብዎትም? አዎ በዚህ ሊደነቁበት! ሊገረሙበትና አልፎ ተርፎም ሊያበሳጭዎት አይገባም!! ረጋ ብለዉ ግን እራስዎን ይጠይቁ፣ ምም እንኳ ከሰዎች ጋር ተገናኝቶ ለመወያየት ወቅቱ አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ለሚናገሩት እያንዳንዱ ቃል ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገዉ ቢረዱትም ደፍረዉ ግን ከሚቀርቡትና ከሚግባቡት ሰዉ ጋር በመወያየት የሁኔታዎችን ምንጭነት ለማወቅ ከመመራመር አይቦዝኑ። የኑሮና የሕይወት ትርጉምም ይህንኑ ያሳየናል። መልካም ጊዜ ሲገኝ እየተዝናኑ መኖር ብቻ ሳይሆን በችግር ወቅትም በችግሩ ዙሪያ እየተወያዩ ለመፍትሔዉ በጋራ መጠበብን ይጠይቃልና!! እንግዲህ ልብ ይበሉ ይህ ወቅት ሰላምን ነጥቆ ወደ ግጭት የሚከት ሰይጣን የፈረጠመበትና የአብሮነታችንና የአንድነታችን ጠንቅ በመሆንም ወደፊት እንዳንጓዝ ሆን ተብሎ ብሔራዊ ጋሬጣ የተዘረጋበት አደገኛ ጊዜ ነዉ።

አሁን ከላይ ያለዉ ስሜትና ሥጋት እንዴትና ለምን ሊፈጠር ቻለ? ብለን እንደገና እራሳችንን እንጠይቀዉ። ካስፈለገም ጥያቄዉን ዘርዘር ማድረግ ይቻላል። እነዚያ መልካም አያቶቻችን የተዉልን የመልካም ባህል፣ ወግና ልምድ ትዉፊቶች አልፎ ተርፎም የብሔራዊ ማንነታችንና የአብሮነታችን ማያያዣ ግማዶች በዚህ በኛዉ በአሁኖቹ ትዉልዶች ስጋት ዉስጥ የወደቀበት ምክንያቱስ ምንድነዉ? በማለት እንመራመር።

<u>**„ይህ አስፈሪ የሚመስል ነገር ግን ለዘላቂነት የማይበጅ ወቅት ለእኛ ለአብሮነታችን አደገኛና አስቸጋሪ ያደረገዉ ማን ነዉ? እንዲሆንስ የተደረገዉ ለምንድን ነዉ? እንዲሆን መደረጉስ ሆን ተብሎ የታቀደና የተቀመመ ሴራ አለበት! ወይንስ! በስህተትና በየዋህነት? አጋጣሚ የፈጠረዉ ነዉ?"**</u> በማለት ረጋ ብለን እራሳችንን እየጠየቅን እንወያይ። ለመልሱም ሩቅ መባዘን የለብንም። ከዚያዉ ከእኔና ከእርስዎ አዕምሮ ዉስጥ ነዉና ሳንደባበቅ በሀቅ እንድንፈልገዉ አሳስብዎታለሁ። ካላገኙት ግን እራስዎን ሚዛን ላይ አላስቀመጡትምና ከእኔ በፊት ህሊናዎ ይታዘብዎታል። የህሊና ፍርድ ደግሞ ምድር ላይ ካሉት ፍርዶች ሁሉ የከፋ ነዉና ይጠንቀቁ። በተጨማሪም ለወደፊቱ አብሮነታችን ዋስትናዉም ይኸዉ የግልጽነት አቋማችን ነዉና ደጋግመን እራሳችንን በመጠየቅ እዉነቱ ጋር ለመድረስ እንትጋ!!

አሁን ወደ ዋናዉ የመወያያ እምብርት እንግባ! ለዚህ ቋንቋን መሰረት ላደረገ የፌደራል የጎሳ አገዛዝ ድጋፋቸዉን ለመግለጽ ሲሉ አንዳንድ ወገኖች ያለምንም መጨነቅ (ማስተዋል) በቀላሉ የሚወረዉሯቸዉን ቃላቶች ሲሰሙ ከማዘን አልፎ ወደ ሌላ ጥያቄም ተገፍትረዉ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ዘልቆ በመሄድ እንዲህ ብለዉ እራስዎን ሳይጠይቁ አልቀሩም ይሆናል፣- <u>ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች በዚህ ትዉልድ አዕምሮ ዉስጥ በቀላሉ የማይጠፉና ወደ ታሪክም የሚሸጋገሩ፣ ወደፊትም በሰሩት ታሪክ ልጆቻቸዉ የሚያፍሩባቸዉ ጎጂና የማይፋቁ መልእክቶችን እያስተላለፉ ስለመሆናቸዉ በዉል ይረዱት ይሆን? ካልተረዱትስ እነሱን ለማሳወቅ ምን ማድረግ ይሻላል? ይህን ለመጪዉ ትዉድ የሚተላለፍ ጠባሳን ከማስተላለፍ እንዲቆጠቡ ለማድረግ ምን የተሻለስ ዘዴ ይኖራል?</u>

አሁን ከእኔ ከዚህ መጣጥፍ አዘጋጅ ጋር ወደሚገናኙበት ክፍል ገብተዋልና እንኳን ደህና መጡ እልዎታለን። ከዚህ በኋላ ዘና ይበሉና በአገራችን ጉዳይ ላይ በመወያየት በንጹህ ህሊና የሚሰጥ ፍርድን ተጋግዘን ለማስተናገድ አብሮነታችንን እየገነባን እንቀጥላለን ማለት ነዉ።

(ለሁላችንም ግንዛቤ እንዲረዳን እስኪ የሚከተለዉን ሠንጠረዥ እንመልከት!)

# ክፍል ፩;- „የወቅታዊዉ ትግል አሠላለፍና የትግል ስልት ሲመረመር“

**የጽሁፉ ዓላማ፣- የትግሉን ዋና ዋና ሃይሎች አሠላለፍና ባህሪያቸዉን በማሳየት ለመፍትሔዉ አፈላለግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ነዉ፣**

## በአገራችን የፖለቲካ ትግል ዉስጥ ያለዉ የሃይል አሠላለፍና ባህሪያቸዉ ሲመረመር

ሀ/

ያለዉን አገዛዝ የሚቃወም የአገር ዉስጥ የለዉጥ ሃይል፣

የተፈጥሮ ስብት ሕግ

ለ/

ያለዉን አገዛዝ የሚደግፍ የአገር ዉስጥ ሃይል፣

የተፈጥሮ የስ በት ሕግ

መ/

ዘረኛዉ አገዛዝ ተወገደም ቀጠለም ብዙ የማያስጨንቀዉና ዋነኛዉ ትኩረቱ የተረጋጋ ኑሮና ሰላም መኖር የሆነ የአገር ዉስጥ ሃይል፣

## 1/ በ „ሀ“ የሚመደቡት ሃይሎች አሠላለፍና ባህሪያቸዉ ሲመረመር)

### 1.1፣- የ „ሀ“ ሃይሎች አሠላለፍ፣-

ሀ/

ያለዉን አገዛዝ የሚቃወም የአገር ዉስጥ የለዉጥ ሃይል፣

ሀ/1

ያለዉን አገዛዝ በትጥቅ ትግል ጭምር የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣

የተፈጥሮ የስበት ሕግ

ሀ/2

ያለዉን አገዛዝ በሰላማዊ ትግል የሚቃወም የለዉጥ ሃይል፣

ሀ/1.1

በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅት መስርቶና ተደራጅቶ የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣ (*) ምሳሌ፣- ግንቦት-7

ሀ/1.2

በሚኖርበት ብሔረ ሰብ ዉስጥ በአርበ ኝነት ትግል ተደራ ጅቶ የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣ (**) ምሳሌ፣- በጎበዝ አለቆች የተደራጀ ሃይል፣

ሀ/2.1

በፖለቲካ ድርጅት ተሰባስበዉ የሚታገሉ የለዉጥ ሃይሎች፣ (***) ምሳሌ፣- ከቅንጅት በኋላ የአንድነት፣ የአረና፣ የኦፌ ዲን የመድረክ መፈጠርና አፈናዉ መጠንከሩ፣

ሀ/2.2

በሙያ ማህበራትና በግል አመጽ ትግል የሚያደርጉ የለዉጥ ሃይሎች፣ (****) ምሳሌ፣- ከ 2009 ጀምሮ የቄሮና የፋኖ ወጣቶች እንቅስቃሴ መጠናከር!

ከጊዜ ወደ ጊዜ የተደረጉት የሕዝብ ትግል ዉጤቶች ማሳያ! (በወቅቱ ያልተፈቱ የማህበራዊ፣ ኤኮኖሚዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ያመጡት ዉጥረትእንዴት እየተወጠሩና አዲስ የትግል ስልትን እየፈጠሩ እንደሚሄዱ ማሳያ)

* - የ1997 ምርጫ በፈጠረዉ ቀዉስ የተፈጠረ ፣ ** - ከሕዝባዊ አመጹ በኋላ የተፈጠረ!

*** ፣- አማራጭ ማጣት የወለደዉ፣ ****፣ - አማራጭ ማጣትና የመሪ ድርጅት መታፈን የወለደዉ፣

**ከጊዜ ወደ ጊዜ የተደረጉ የሕዝብ ትግል ዉጤቶች ማሳያ (የችግሮች አለመፈታት ያመጣዉ)ሠንጠረዥ፣**




**ደረጃ 1**፣- 1983 ዓ/ም - የሥርዓት ለዉጥ (የደርግ መወገድና የህወሐት/ኢሕአዴግ) ሥልጣን መቆጣጠር፣፡ የአገር አንድነት መናጋት፣ የሲቪል ማህበራት ህልዉና ችግር ዉስጥ መግባት፣ የዘር ግጭት ባመጣዉ ጦስ የዜጎችመሞትና መፈናቀል (አርባጉጉ፣ በዴሳ፣ ገለምሶ..)፣ወዘተ....

**ደረጃ 2** ፣- 1989-1993 ዓ/ም የኢትዮጵያና ኤርትራ ቁርሾ መባባስ፣ የጦርነት መቀስቀስና የ70 ሺህ ዜጎች ማለቅ፣ የህወሀት የእርስ በእርስ መከፋፈልና መወነጃጀል መከሰት፣ ወደ አንድ ሰዉ አምባገነንነት ማምራት፣

**ደረጃ 3**፤- 1997 ዓ/ም - የዴሞክራሲ መብቶች መፈንጠቅ፣ የልዩ ልዩ የኤኮኖሚ አዉታሮች ግንባታ እድገት መታዬትና የኑሮ ዉድነት መጨመር፣ የፓርቲዎች በነጻነት ለምርጫ ዉድድር መንቀሳቀስ መጀመር፣ በመጨረሻም የምርጫ ሂደቱ መኮላሸትና የዲሞክራሲ አፈና ጅማሮ፣ ሕዝብ በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ እምነቱን ያነሳበት፣ የፖለቲካ ቀዉስ መጀመርና የአንድ ሰዉ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መተካት....ወዘተ.

**ደረጃ 4**፤- 2002 ዓ/ም - የሕዝብ አመኔታ የነባቸዉና የጎለበቱት ፓርቲዎች መኮላሸትና መታፈን፣ የስለላ መዋቅሩ ክትትል መጠናከር፣ የአንድ ሰዉና ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ መበርታት፣ የልማት ግንባታዎችን በህወሀት ሥር አድርጎ የመቆጣጠር ስልት መጠናከር፣ የዜጎች መገፋትና የኑሮ ዉድነቱ መናር፣ የሙሰኛነት ወንጀል መግነንና አላግባብ በሥልጣን መጠቀም መስፋፋት፣ የብሔረሰቦች እርስ በእርስ መከፋፈልና መራራቅ መቀጠል፣ በመላዉ አገሪቱ የህወሐት አገዛዝ በወሳኝነት ተጠናክሮ መምጣት፣

**ደረጃ 5**፤- 2007 ዓ/ም ፤- የህወሀት የበላይነት ገኖ መዉጣት፣ ሕዝብን በመናቅ የምርጫ ዉጤትን በ96 ፐርሰንት መንጠቅ፣ የሕዝብ ብሶትና የብሔረሰቦች መብት ጥያቄ ተጠናክሮ መምጣትና የሕዝባዊ አመጾች ማቆጥቆት፣

**ደረጃ 6**፤- 2008–2010 ዓ/ም የሕዝቡ በፓርቲዎች አመራር ተስፋ መቁረጥና በአዲስ ስልት የሕዝባዊ የለዉጥ እንቅስቃሴ መቀጣጠል፣ የ መጠናከር፣

**ደረጃ 7**፤- ከታህሳስ 2010 ጀምሮ -የተጠናከረ ሕዝባዊ የለዉጥ ፍላጎት መጨመርና በግጭቶችም የሰዉ ሞትና መፈናቀል መባባስ፣ የአገራችን የፖለቲካ ቀዉስ መስፋትና በህወሀት መራሹ ኢሕአዴግ ሥር ያሉት ብአዴንና ኦህዴድ አንድነት መፍጠርና ኢትዮጵያዊነትን የመፈለግ አቅጣጫ መያዝ፣ በዩኒቨር ሲቲዎችና በስፖርት ቦታዎች የዘር ግጭት መከሰትና የተማሪዎች ሞት መስፋፋት፣ በሶማሌና በኦሮሞ ክልሎች የዘር ጥቃት መከሰትና የዜጎች መሞትና መፈናቀል፣ የአገራችን አቅጣጫ በመስቀለኛ ጎዞ ላይ መሆን፣ የሕዝብ የኑሮ ሥጋት መባባስና የኑሮ ዉድነትም መናር፣ የዉጭ የፖለቲካ ግንኙነቱ እያሽቆለቆለ መሄድ፣ የሥርአት ለዉጥ ጥያቄዉ ከሕዝብ እየገፋ መምጣቱና ሕዝባዊ ትግሉ በአገር አቀፍ ደረጃ ተናቦና ተባብሮ እንዲቀጥል የሚያሳስብ ጥያቄ መበራከት መጀመሩ፣ የህወሀት ሥጋትና አፈና መጠናከርና ሶስት ወራት በፈጀ ግምገማ መጠመድና የጥንቱን የጫካ መዋቅሩን መመለስ፣ ታህሳስ 2010 ዓ/ም መጨረሻ የኢሕአዴግ ስብሰባ መካሄድና ልዩነት እንዳለ በጠቅላይ ሚንስትሩ መገለጽ፣ በመጨረሻም ምንም መፍትሔ ባልጠቆመ (ሁሉን አቀፍ የፖለቲካ ዉይይትና ብሄራዊ እርቅ እንዲደረግ የሚያበስር መግለጫ ሲጠበቅ ! ነገር ግን አመጽን ለማፈን ብቻ በተዘጋጀ መግለጫ ስብሰባዉ መጠናቀቁን ጠቅላይ ሚ/ መግለጻቸዉና በቀናት ልዩነት ደግሞ፣ ታህሳስ 26/2010 ዓ/ም (ጃንዋሪ 4 2018) እስረኞችን ለመፍታት መስማማታቸዉን አሁንም ጠቅ.ሚ/ መግለጻቸዉ፣ ወዘተ....

## 1.2- የ „ሀ“ ለዉጥ ሃይሎች ባህሪያት ሲመረመር (አሁን ያለዉ)፣

**ሀ/1**

| ያለዉን አገዛዝ በትጥቅ ትግል የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣ |
|---|

1/ ችግሩ አሳስቦትና ሁኔታዉ አስገድዶት (አማራጭ በማጣት) መሣሪያ ያነሳ ስብስብ፣

2/ የሕዝብን የለዉጥ ፍላጎት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከአገዛዙ የጦር ሃይልና ከስለላ ቡድኖቹ ጋር ለመፋለም፣ ለመቋቋም፣ ለመሰቃየት፣ ለመግደልና ለመሞት የቆረጠ፣

2/ የድሉን ትክክለኛ ጊዜ ባያዉቀዉም ዋነኛ የለዉጥ መሪ በመሆን የሕዝቡን ትግል ዳር ለማድረስ እራሱን ለሕዝብ አሳልፎ የሰጠና ፣ ትግሉን የሚያስተባብር፣

3/ ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም በማለት ኑሮ ከሚፈጥረዉ ችግር ጋር ሁሉ ለመፋለምና፣ ለመቋቋም የቆረጠ፣

4/ ተመሳሳይ አላማ ካላቸዉ ተጋዮች ጋር መተባበርና ትግሉን የተናበበ እንዲሆን ማድረግ ከቻለ ለድሉ ቅርብ የሆነ፣

5/ የተሟላ የሕዝብ ድጋፍ ስላለዉ ከአገዛዙ ታጣቂዎች በተሻለ የሞራል ደረጃ የሚገኝ። በሳል ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር ካለዉ ደግሞ አገዛዙን ለድርድር ማስገደድና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን እዉን ለማድረግ የሚችል፣

6/ ለድል (ለስልጣን) ከበቃ በኋላ የሚፈጠረዉን ፖለቲካዊ ሁኔታ ማወቅ ስለሚያስቸግር የሕዝብ ክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልገዉ። ለዚህም በሂደት ከየብሔረሰቡ የሚገኙ እዉቅ ዜጎችና የፖለቲካ ምሁራን ሊያስቡበትና ሊመክሩበት የሚገባ ሃይል ነዉ። <u>(አሁን በአሜሪካ የተፈጠረዉ የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄም ይህን አደገኛ ክፍተት ለመሙላት የሚንቀሳቀስ አስፈላጊ ስብስብ ይመስላል።)</u>

## <u>*ሀ*/1.1</u>

<u>በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅት መስርቶ በአጎራባች አገራት የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣</u>

<u>**ምሳሌ**</u>፣- <u>ግንቦት-7</u>

### <u>ከ „*ሀ*/1“ በተጨማሪ (በተለዬ)፣-</u>

1/ ከ1997 የምርጫ ቀዉስ በኋላ ሰላማዊ ትግል ብቻዉን እንደማያዋጣ በማረጋገጥ ተገዶ የመሳሪያ ትግልን የጀመረና የፖለቲካ ትግልን ወደ ጠነከረ ደረጃ ያሸጋገረ፣

2/ተመጣጣኝ ተዋጊ ሃይል እስከሚኖረዉና ሰፊ የትግል ወረዳን መቆጣጠር እስከሚችል ድረስ የጎሬላ ትግል ስልትን ለማካሄድ የሚገደድ፣ ለዚህም የበሰለ ወታደራዊና ፖለቲካዊ አመራር የሚያስፈልገዉ እንዲሁም የህወሓትን ጠንካራና ደካማ ጎን መከታተልና ማጥናት ግድ የሚለዉ።

3/ የዉጊያ ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያስችለዉን መረጃ ለማሰባሰብ አድካሚ ስለሚሆንበት የተለዬ የመረጃ አሰባሰብ ስልት የሚያስፈልገዉ፣

4/ ትግሉ እየጠነከረና ድል እየጨመረ በሄደ ቁጥር የከፋቸዉ የአገዛዙ ጦር አባላት እየከዱ የሚቀላቀሉትና የድሉ ጊዜ  የሚፋጠንለት ሃይል ነዉ፣

5/ የሚታገልበት አካባቢ (የተጠጋበት ፖለቲካ፣ የአካባቢዉ ሕዝብ ድጋፍ፣ የሚታገልበት አገር ፖለቲካዊ ሁኔታ ወዘተ የትግሉን ሂደት ሊወስኑበት ስለሚችሉ ድንገተኛ የአደረጃጀት ለዉጥ ወይም የህልዉና መፈታተን ሊፈነዳበት የሚችል፣

## <u>*ሀ*/1.2</u>

<u>በሚኖርበት ብሔረ ሰብ ዉስጥ በአርበ ኝነት ትግል ተደራ ጅቶ የሚፋለም የለዉጥ ሃይል፣</u>

<u>**ምሳሌ**</u>፣- <u>በጎበዝ አለቆች የተደራጀ የአርበኝነት ትግል፣</u>

### <u>ከ „*ሀ*/1“ በተጨማሪ (በተለዬ)፣</u>

1/ በኦሮሞና በአማራዉ ሕዝብ ዉስጥ የምሬት አመጽ ከተፈጠረበት ከ 2008 ዓ/ም-2009 (2015/2016 እኤአ) በኋላ የተከሰተ ከ 1997 ቀጥሎ የትግሉን መክረርና ማደግ (በተፈጥሮ ሕግ መሰረት የትግሉ ጸባይ መቀየርን) ያረጋገጠ፣ አገዛዙንም ያስደነገጠ፣

2/ ትግሉ መራራና ለአካባቢዉ ሰላማዊ ሕዝብም አደገኛ የሆነ ቢሆንም ወሳኝነት ያለዉን ትግል ለማካሄድ ግን ከዚህ ሌላ አማራጭ በመጥፋቱ የተፈጠረና ነገር ግን የበሰለ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር የሚፈልግ፣

3/ የአገዛዙ ጥንካሬና የስለላ ክትትል ካልሆነ በስተቀር የዉጭ ተጽእኖ ትግሉን ሊያከሽፈዉ አይችልም፣ ይሁን እንጂ በቁ/2 እንደተገለጸዉ ከፍተኛ የሆነ የትግል አጋርነትና የበሰለ አመራርን የሚፈልግ፣

4/ የመረጃ አሰባሰብ፣ ከአጋር አርበኞች ጋር የሚደረገዉ የትግል ትብብርና እንዲሁም የስንቅና ትጥቅ አቅርቦቱ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅበት፣

5/ ከሌሎች ብሄረሰብ አርበኞች ጋር እስካልተባበረ ድረስ ትግሉ ሊመታ(የድል ጊዜዉ ሊርቅ) የሚልበት፣

6/ ይህ ሃይል በድል ከዘለቀ ሌላ የእርስ በእርስ አዙሪት ዉስጥ አገሪቱ ላለመግባቷ መተማመኛን የማይሰጥ! በመሆኑም የሕዝብ ክትትልና ተጠያቂነትን የሚፈልግ፣

7/ ይህ ሀይል ዘመናዊ የዉትድርና ስልጠና ባይኖረዉም በወኔና በአገር ፍቅር ስሜት የተነሳ ስለሆነ ለድል ቅርብ ነዉ። ነገር ግን ከ *ሀ*/1.1 (ማለትም በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅት መስርቶ በአጎራባች አገ ራት ከሚፋለመዉ የለዉጥ ሃይል) ጋር የትግል ትብብር መስርቶ መታገሉ የበለጠ የሚያዋጣዉ፣

10/ በተራ ቁ/ 9 የሰፈረዉ የትግል አጋርነት ወደፊት ችግር እንዳይፈጥር ሕጋዊ መላ የሚፈልግ።

11/ ትግሉ እየተጠናከረ በሄደ ቁጥር የወያኔ ጦር አባላትም እየከዱ እንዲያጠናክሩት ሁኔታዉ ግድ ይላል፣

## ሀ/2

**ያለዉን አገዛዝ በሰላማዊ ትግል የሚቃወም ሕዝባዊ የለዉጥ ሃይል፣**

1/ ከአጀማመሩ ነጻነትን የናፈቁ ዜጎች የተሰባሰቡበት ሃይል ሲሆን ዓላማዉም ሠላማዊ በሆነ መንገድ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን የጣረ፣
2/ ከ 1997 ምርጫ በኋላ አገዛዙ በፈጠረዉ የአፈና ስልት እንዲሽመደመዱ የተደረጉና ሕዝቡ ዉስጥ ገብተዉ ፖለቲካዊ ሥራ ለመሥራት ባለመቻላቸዉ ድንገት የሚፈነዳን የአመጽ ትግል ብቻ በአማራጭነት እንዲጠብቁ የተገደዱ፣
3/ የዘር ፖለቲካዉ በፈጠረዉ ተንኮል ምክንያት በሕዝቡ ዉስጥ መከፋፈልና መጠራጠር በመፈጠሩ ሕዝቡ አብሯቸዉ ለመብቱ እንዲጮህ ለማድረግ ያልቻለ (እንዳይችል የተደረገ)፣
4/ በአመጽና በዝምታ የሚካሄዱ ትግሎች ብቻቸዉን ለድል እንደማያበቁ የተረዳና አገዛዙን በሃይል ለማስጨነቅ ነፍጥ ያነሱ አርበኞችን ትግል ለመተባበር ፈቃደኛ የሆነ (የሚገደድ)፣
5/ አገዛዙ ተገዶ ወደ ድርድር በሚመጣበት ወቅት ሕዝብን ወክሎ ለመደራደርና ፖለተካዊ እርቅ አድርጎ የተረጋጋ ዴሞክረሲያዊ መሠረት ለመጣል የሚያስችል አማራጭ ሃይል የሚሆን፣
6/ ለህወሓት አገዛዝም የዚህ ተቃዋሚ ሃይል መኖር የሚያስፈልገዉ። (አንደኛ ሃይለኛ ታጋዮችን ያጠምድበታል፣ ሁለተኛ ለዉጭ ፖለቲካ ፍጆታዉ ይጠቀምበታል፣) ይሁን እንጂ በተቃራኒዉም አገዛዙን ፍርሃት (ሥጋት) ዉስጥ የከተተ፣
7/ አገዛዙ ተገዶ ሲንበረከክና ለድርድር ሲዘጋጅ ወይም ከተሸነፈ በኋላ የሽግግር መንግሥትን ለመመሥረት ሕዝብን ማደራጀት የሚችል፣ (ሕዝብን ወክሎ ለመደራደር አስፈላጊ ሃይል የሆነ) በዚህም አገሪቷ መንግሥት አልባ እንዳትሆን የሚረዳ ሀይል ነዉ።

## ሀ/2.1 ከ „ሀ/2 " በተጨማሪ (በተለዬ)፣

**በፖለቲካ ድርጅት ተሰባስበዉ የሚታገሉ የለዉጥ ሃይሎች፣**

**ምሳሌ፣-** መድረክ፣ አንድነት፣ ኦፌኮ፣ አረና ወዘተ....

1/ ነጻነትን የናፈቀ ቢሆንም በነጻነት ለመታገል ግን ያልቻለ (አፈና ያለበት)
2/ አገዛዙ በሚፈጥራቸዉ ተለጣፊ በሚባሉ ድርጅቶች ሳቢያ ሰላማዊ ትግሉ እየተኮላሸበት በመዉደቅና በመነሳት ላይ ያለ፣
3/ አገዛዙ ከፍተኛ ክፍያ በማድረግ በሚያሰማራቸዉ ሰላዮች ምክንያት አመራሩና አባላቶቹ በከፍተኛ ስጋትና አደጋ ላይ የሚገኙበት፣ ለእስራት፣ ለስደትና ለሞት እየተዳርጉ ምሬትና አጣብቂኝ ዉስጥ የገባ ሃይል፣
4/ አገዛዙን ፊት ለፊት ለመታገል ችግር (ፍርሃት) ያለበትና በዚህም ምክንያት ሕዝብ ተስፋ የማይጥልበትና የማይተማመንበት፣
5/ ነጻነቱን ሊያመጣለት የሚችል አስተማማኝ ድርጅት ካገኘ ለመደገፍና ለመቀላቀል የማያቅማማ፣
6/ ከመሰል ድርጅቶች ጋር ለመሥራት ብቃት ያጣ ወይም የተቸገረ፣

## ሀ/2.2 ከ „ሀ/2" በተጨማሪ (በተለዬ)

**በሙያ ማህበራትና በግል አመጽ ትግል የሚያደርጉ ህዝባዊ የለዉጥ ሃይሎች፣-** የቄሮ፣ ፋኖ እንቅስቃሴ መጠናከር፣

1/ በሙያ ማህበራት፣ በመስሪያ ቤቶችና በዜጎች መኖሪያ አካባቢ የሚታዩትና የሚሰሙት ብሶቶች መጠንከር የዚህ ሃይል መገለጫ ባህሪያት ሲሆኑ፣ አገዛዙ ተገቢዉን መፍትሔ እስካልፈለገ ድረስ የአመጽ ትግል ሊፈነዳበት የሚችል፣
2/ አገዛዙንና ተባባሪዎቹን ሥጋት ዉስጥ የሚከትና የሚያነጫንጭ ድምጾች የሚሰሙበት ሃይል።( ባለፈዉ ሰሞን በመምህራን ማህበራት አካባቢ የተሰሙት የብሶት ድምጾች ሁሉ የዚህ ነባራዊ ሁኔታ ማስረጃዎች ናቸዉ።)
3/ የሕዝብ አመጽ ከቁጥጥር ዉጭ በመሆን የብቀላ እርምጃዎች እንዳይፈጠሩ አገዛዙ የእርቅን መንገድ መከተል እንዳለበት የሚመክርና የሚያሳስብ ሃይል ያለበት፣
4/ የአገሪቱን ችግር የተረዱና መፍትሔዉንም ሊጠቁሙ የሚችሉ አዛዉንቶችና የፖለቲካ ምሁራን ሁሉ የሚገኙበት ሃይል በመሆኑ አገዛዙ ካወቀበት ከሕዝብ ጋር ታርቆ ሰላማዊ ሽግግር እንዲከናወን ሊረዳዉ የሚችል ጠቃሚ ስብስብ የሚገኝበት ሃይል ነዉ።

## ማሳሰቢያ!

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየዉ „የተፈጥሮ የስበት ሕግ!“ የሚል ይነበባል። ይህ ማለት፣-

1/ ከተፈጥሮ ሳይንስ እንደምንረዳዉ ሁሉም ነገር በተቃራኒ ገጽታዎች የተሞላ ነዉ። ጥቁር ከነጭ፣ አጭር ከረጅም፣ ወፍራም ከቀጭን ሀብታም ከድሃ፣ወዘተ..በጸባይና በስሜት አፈጣጠርም የዋህ ከፉ፣ አዛኝ ጨካኝ፣ ዉሸታም ሀቀኛ፣ ጎበዝ ሰነፍ ስግብግብ ቁጥብ፣ አስተዋይግዴለሽ፣ወዘተ እያለ ይቀጥላል።

እንግዲህ እነዚህን የሰዉን ልጅ የተፈጥሮና የዉስጣዊ ስሜቶቻችን ዉጤቶች የሆኑት ደግሞ በእለት ከእለት የሥራ ወይም የተግባር እንቅስቃሴአችን ዉስጥ እያስገባን ለመመርመር ብንሞክር በአንድ አገር ዉስጥ በሚካሄድ ማህበራዊ ተሳትፎ ዉስጥ ከፍተኛ መጠላለፍን ወይም መሳሳብን ሊፈጥሩ የሚችሉ ክስተቶችን እናገኛለን። በዚህም ምክንያት የሚካሄዱት የፖለቲካ ትግሎች ሊፋጠኑ ወይም ሊዘገዩ ወይም ሊዳፈኑ ይችላሉ። ከዚህም በቀር የሕዝብ አመለካከት አስማምቶና በአንድ ዓላማ ሥር አግባብቶ ለማታገል ችግር ይፈጠራል  ማለት ነዉ። በመሆኑም የስበት ሕግ የሚለዉ እዘኒህን በስሜቶቻችን መለዋወጥ ምክንያት የሚፈጠሩትን ብዥታዎችና ክስተቶች ለመጠቆም ሲባል የተጠቀምንበት ነዉ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

(ለአስተያየት፣- yoha2010@hotmail.com)

## በቀጣይ ክፍሎች የምንመለከታቸዉ ነጥቦች

1.3./ በዉጭ አገር የ „ሀ“ ደጋፊ ሀይሎች (ሀሁ) አሰላለፍና ባህሪያት ሲመረመር፣-

2/ በ „ለ“ የሚመደቡት ሃይሎች አሠላለፍና ባህሪያቸዉ ሲመረመር፣-

2.3፣- በዉጭ አገር የ „ለ“ ደጋፊ ሃይሎች (ለሉ) አሠላለፍና የትግል ባህሪያት ሲመረመር፣-

3- በ „መ“ የሚመደቡት የአገር ዉስጥ ሃይሎች አሠላለፍና ባህሪያቸዉ ሲመረመር፣-

3.3፣- በዉጭ አገር የ„መ“ አቋም የሚከተሉ ሃይሎች (መሙ) አሠላለፍና የትግል ባህሪያት፣-

ክፍል ፬፣- በተለይ - የህወሓት ሃይል (አገዛዝ) ለብቻ ሲመረመር፣-

ክፍል ፫፣- አዎ! በእርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥርዓት (የመንግስት) ለዉጥ ያስፈልገዋል!

ክፍል ፬፣- አገራችን ከገባችበት ችግር እንድትወጣ ለመርዳት በጋራ የምንቆምለት የመፍትሔ ሀሳብስ የትኛዉ ሊሆን ይገባል?

ክፍል ፭፣- የወቅቱ አማራጭ ሕዝባዊ አመጹ በመሳሪያ ትግልም መታገዝ አለበት ከሆነ! ታዲያ  እንዴት ማገዝ ይቻላል?

ክፍል ፮- ከድል በሗላ ያለዉ ፍላጎታችንስ (ግባችን) ምንድን ነዉ?

ክፍል ፯፣- በሕዝባዊ ትግሉ ዉስጥ የዉጭ ሀይሎች ሚናና ተጽዕኖ ሲፈተሽ፣

